# ማድመጥ ያልቻለ አድማጭ ያጣል

(የዶር ጌታቸው በጋሻውን ጽሁፍና ፓል ቶክ ውይይት አስመልክቶ)

በአሉላ (alulla2@yahoo.com)

*"ኦነግ ተገንጥዬ ነፃ ኦሮሚያ አቋቁማለሁ የሚል official አቋም መኖሩን አላውቅም።" ዶር ጌታቸው በጋሻው።*

ሰላም ውድ አንባቢያን ወገኖቼ፡

ዶር ጌታቸው በጋሻው በነሐሴ 7 ቀን 2003 ዓ.ም. (August 12, 2011) "የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ፤ ከኦነግና ሌሎች የዘር ድርጅቶች ጋር መነጋገር መተባበር ለምን ያስፈልጋል?" በሚል ርዕስ ለንባብ ያቀረቡትን ጽሁፍና በቀጣይነትም ዕሁድ ነሐሴ 9 ቀን 2003 ዓ.ም. (August 14, 2011) በራስ አሉላ አባ ነጋ የፓል ቶክ መወያያ መድረክ በመቅረብ በጽሁፋቸውና የወቅቱን የግንቦት 7፡ ኦነግና ኦብነግ የጋራ ትብብር አስመልክቶ ለቀረበላቸው በርካታ ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ መሠረታዊውንና መታየት ይገባዋል የምለውን አወዛጋቢ ነጥብ ለማቅረብ እሞክራለሁ (አባሪውን ገጽ 8 ይመልከቱ)።

ዶር ጌታቸው በጋሻው በጽሁፋቸው መደምደሚያ ላይ "ይህንን የጋራ ጥረት በክፉ ዓይን እየተመለከታችሁ ያላችሁት አሉታዊ ኃይሎች፤ የባቡሩን ሀዲድ ለመጠምዘዝ ከመሞከር ባቡሩ ላይ ለመሳፈር ሞክሩ፤ ቀይዶ የያዛችሁ ችግር የሚፈቅድላችሁ ከሆናችሁ።..." በሚለው መደምደሚያቸው የተለየ ሀሳብ ማድመጥ ባይፈልጉም ለህዝብና ለምዬ ኢትዮጵያ ስል ብዕሬን ላነሳ ተገድጃለሁ። በሀገር እልውና ላይ ያንዣበበ አነጋጋሪ ሁኔታ እንደ ሀሳብ ልዩነት ከታየም፡ ሌሎች የሚሰነዝሩትን ሀሳብ እንደማከብር ሁላ የእኔንም "ኢትዮጵያችን አንድነቷን ጠብቃ የሰው ልጅ ያልተገደበ መብት የተከበረባትና ሀገር የሁሉም ልጆቿ ትሆን ዘንድ" ከአለኝ ጽኑ ፍላጎት አንጻር የማቀርበውን እንደ ሀሳብ ትቀበሉት ዘንድ መልካም ነው እላለሁ። በተጨማሪም አንዱም በመደገፍ ሌላውም በመቃወም የሚጽፈውን ብዙ አንባቢ አለውና የተነሳው ጉዳይ፡ የሚነሱ ጥያቄዎች፡ በግልጽ እንዲታዩና ሌላውም ከሁሉም አቅጣጫ የሚቀርቡትን አብላልቶና አገናዝቦ "ምን መደረግ አለበት?" ለሚለው ምላሽ የሚሰጥበት ጊዜ እያመለጠ በመሆኑ እንደርስበት ዘንዳ ያበረታታል ያነቃቃል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁኝ።

"... ያለው ሀዲድ አንድና አንድ ብቻ ነው፤..." በሚለው የዶር ጌታቸው መደምደሚያ ሌላ አትተንፍሱ፡ አትናገሩ፡ አትጻፉ እጅጉን ያሳዝናል ያስተዛዝባል። እኛ ደግሞ ዓይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ፡ ከኔ በቀር ሌላ አትመኑ ሂደታቸውን እየተስተዋለ የማለት የዜግነት ግዴታችን የሚሆነው የተምታታ መልዕክታቸውን ጠርጥሮ ማውጣት ጠቀሜታ አለውና እስቲ ትንሽ ልበል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በቀጣይነት ከወያኔ ውድቀት በኋላ የህዝብንና የሀገርን ኃላፊነት ለመሸከም በትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በሞላ: የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን በቀና መንፈስ በትግል ላይ እያሉ ማንሸራሸር ካልቻሉና እኔ የያዝኩት ባቡር ብቻ ከሆነ ነገሩ "ፈጣን ነው ባቡሩ…ባ…ቡ..ሩ…ፈጣን ነው ባ…ቡ…ሩ…" ከተዘፈነለት የደርግ "ዴሞክራሲ" የተሻለ አማራጭ ማምጣታቸው ያጠራጥራል።

ዶር ጌታቸው በጋሻው በነሐሴ 9 ቀን 2003 ዓ.ም. በራስ አሉላ አባ ነጋ የመወያያ ፓል ቶክ ክፍል ቀርበው የቀረበላቸውን ጥያቄና የሰጡትን ምላሽ አንተርሶ የታዘብኩትንና ሌላውም ወገን ማድመጥ አለበት በማለት ከድምጽ ቅጂው የተወሰደውን ቅንጣቢ፡ በጽሁፍ ጭምር አያይዤ አቅርቤሃለሁ።

ዶር ጌታቸው፡ "እኔ፤ በኦነግ ውስጥ ብዙ የሚያበረታቱ ለውጦችና እድገቶች ይታየኛል። አዲስ አመለካከት፤ አዲስ ራእይ፤ አዲስ ኃይል አሰላለፍ እየመጣ መሆኑን እሰማለሁ፤ አያለሁ። የኦሮሞን ጥያቄ ዴሞክራሲያዊ በሆነች ኢትዮጵያ ውስጥ ለመፍታት ይቻላል የሚል አመለካከት እየሰፋና እያደገ መጥቷል።…" የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ገጽ 8

ዶር ጌታቸው አለ የሚሉት ለውጥ፡ አመለካከት፡ ራእይ ኦነግ ለአባላቱም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መግለጽ ምን አቃተው? እሳቸው አለ የሚሉት ለውጥና እድገት ለምን ለሌሎቻችን አልታይ አለ? ወይስ ለውጥ ያሉት ይሄን ከሆነ እስቲ በኦገስት 06, 2011 ኦነግ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጽ/ቤት ከጻፈው ልግለጽ

"…the OLF is legitimate organization leading the Oromo people's national struggle against the colonial regime of Ethiopia…."

For more than a century and half, the Oromos have lived under the brutal colonial rule of the Abyssinian/Ethiopia,…

The Oromo people's struggle for freedom is a natural outcome of occupation by alien force, the Ethiopian regime…." Oromo Liberation Front, 09-06-2011 letter to Secretary General of the United Nations.

ይህ ከላይ የተገለጸው ደብዳቤ እንግዲህ ዶር ጌታቸው ጽሁፋቸውን (ጽሁፋቸው ላይ ቀን ባይጽፉበትም ዓርብ ነሐሴ 7 ቀን 2003 ዓ.ም. (August 12, 2011) በኢትዮሚዲያ ድረ ገጽ ወጥቷል) ከማውጣታቸው ቢያንስ ከ6 ቀን በፊት የተላከ ነው። መቼም የኦነግን የአመለካከት ለውጥና አዲስ ራዕይ የተገለጸላቸው ይህን ደብዳቤ ከማንም በፊት እንደሚያገኙት በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ይህን በቅኝ ከያዘችን ኢትዮጵያ ለመገንጠል ነው ትግላችን የሚል መልዕክትን የያዘ ደብዳቤ አስቀድመው ተመልክተው እንኳ "አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ" እንዲሉ አቁን ሸፋፍነው ሊሰብኩን ሲሞክሩ እጅጉን ያሳፍራል። ወይስ ደብዳቤው ሾልኮ አይወጣም ብለው ገምተው ይሆን?

ከኦነግ ደብዳቤ አሁንም እንደምንረዳው፡ የኦነግ አላማ ኦሮሚያን ቅኝ ከያዘችው ኢትዮጵያ ነጻ ማውጣት ነው በአጭሩ።

ዶር ጌታቸው በጋሻው ከላይ ያነሳሁትን ጥያቄ ያብራሩ ዘንድ ዕሁድ በ08/14/2011 በራስ አሉላ አባ ነጋ መወያያ ፓልቶክ ክፍል ቀርበው ተጠይቀው ሲመልሱ፡

"ይህ የኦነግ ደብዳቤ አሳክኮኛል…" ብለዋል

ቀጥሎም "እኔ በኦነግ ውስጥ አለ የምለው ለውጥና ዕድገት…" ይሉና "እንግዲህ ግልጽ ለማድረግ አቶ ዳውድ ይብሳ የሚመሩት አንድ wing አለ የOLF፡ ሌላ በጀነራል ከማል ገልቹ wing አለ። ይኼ በዚህ በጀነራሉ በኩል ካለው ሲመጣ አላየሁም። ይህ የጀነራል ከማልን አዲስ መስመር እንከተል" ይሉናል። "ይህ ኃይል ወደ እኛ መጥቷል፡ ይህንን ኃይል ማለቴ ነው።" ይሉናል።

በመጀመሪያ ደረጃ አሁንም በድጋሚ ዶር ጌታቸው በማንም ድርጅት ውስጥ አለመስማማት፡ መለያየት፡ መከፋፈል ሲኖር እራሱ የድርጅቱ አካሎች ቢያሳውቁ አግባብ ነው ባይ ነኝ። እስከዛሬ በወሬ ደረጃ ይወራል እንጂ የትኛውም የኦነግ ክፍል "ለውጥ አድርጌሃለሁ"፡ ወይም "በነዚህ በነዚህ ጉዳዮች ባለመስማማታችን ተከፋፍለናል"፡ "ኦነግ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለብን ጥያቄውን አንስቶ በአዲስ መስመር ተሰልፏል" ወዘተ. ወዘተ. የሚል መግለጫ በጽሁፍም ሆነ በድምጽ ከማንም ኦነግን ወክልኩ ከሚል ወገን አልተደመጠም። ታዲያ ዶር ጌታቸው ከጓደኞቻቸው የሚያወሩትን ምኞት ለምን "እመኑኝ፡ በኔ ይሁንባችሁ"፡ ውትወታቸው በዛ። በኢሕአፓ ውስጥ ከነበራቸው ተመክሮ የፈጠሩት ኦነግ ዴ (OLF D) ከአለም ያሳውቁንና እንደ ፕሮግራማቸውና እንደ አዲሱ አካሄዳቸው እንደግፋቸው ወይም እንቃወማቸው።

የኦነግንም ሆነ የኦብነግን የመገንጠል ጥያቄአቸውን ወደ ጎን አድርገው በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ያለውን ችግር በጋራ ለመፍታት ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ጋር በጋራ ለመምከር ከተነሱ ማንም የሚከፋ አይኖርም። የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት እንደገና መታደስ ለሀገር ዕድገትና ብልጽግና አስፈላጊነቱ አጠራጣሪ ባይሆንም በትንሹ ለ20 ዓመት በሀገራችን የተተከለ የዘር ድርጅትንና ዘረኝነትን በአንድ ጀምበር ማስወገድ እንደማይቻል አብዛኛው ሊስማማበት ይችላል። የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰችን ባህል፡ ቋንቋ፡ ቅርስ፡ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ሀብትነቱን በመገንዘብ በግልም በቡድንም ለመንከባከብ፡ ለመጠበቅ ለማዳበር የዘር ድርጅቶች ጠቀሜታነት ቢኖራቸውም፡ ኢትዮጵያዊነት ላይ ሲያነጣጥሩ ነው ጠባብ የሚል ተቀጥላ የሚወጣላቸው። ለዚህም ነው የወያኔ ጠባብ የዘረኝነት ፖሊሲ በሌሎች ሳይደገም ሊያበቃ፡ ልንታገለው ይገባል የሚባለው። በአንጻሩም ይህ የዘር ፖለቲካ ለሀገራችን ያስከተለውን ቀውስ ከግምት በማስገባት፡ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባትና ወያኔ የቀበረውን ብሔራዊ ስሜትን ለማደስ በተለይ ተማርን ካሉ ምሁራን ብዙ ይጠበቃል። በወያኔ ዘመን የተወለዱ ሕፃናት የአሁን ወጣቶች፡ በየአካባቢው፡ በየትምህርት ቤቱ፡ በየስብሰባው፡ በየጨዋታው፡ በየድራማው ኢትዮጵያዊነታቸውን

እንዳያውቁና ማንነታቸው በዘረኝነት ላይ ይሆን ዘንድ በትንሹ ለ20 ዓመት የተጣለባቸውን የዘረኝነት አባዜ ይስተካከል ዘንድ መሠረቱን መዘርጋት ሲጠበቅ አንዳንዶች መልሰው በዘር ፖለቲካ ስንቦራጨቁ ማየት አሳፋሪና አሳዛኝ ነው።

ዶር ጌታቸው ትላንት በቨርጂኒያ የግንቦት 7 እና ኦነግ ስብሰባ ላይ ኦነግን የማይደግፍ አንድም የኦሮሞ ተወላጅ አይገኝም ያሉት ወራት ሳይቆጠር በዕሁዱ የፓል ቶክ ስብሰባ ደግሞ ኦነግ ተከፋፍሏል፣ በውስጣዊ ችግር ተደምጧል፣ ከማለትም አልፈው አንደኛውን ወገን ከልካሻ፣ ጊዜው ያለፈበት፣ እያሉ ሲረግሙ ተደምጠዋል። ስለ ኦነግ ውስጥዊ ችግር የሚጠቁመው ጽሁፋቸው እንዲህ ይነበባል።

ገጽ 7፡ "…ኦነግ የራሱን ውስጣዊ ችግር ተወጥቶና ከኤርትራ ቁጥጥር ራሱን አላቆ ብዙ ጊዜ ቃል የሚገባውን የትጥቅ ትግል ከጀመረ በአገራችን ውስጥ የፖለቲካ ጨዋታውን የሚለውጥ ግዙፍ የፖለቲካ ኃይል እንደሚሆን አልጠራጠርም። ወያኔ አሁን ባለው መልኩ ለመግዛት ካቃተውና አገሪቱን ወደ መቆራረስ ዓላማው ከዞረ ለኦነግ የሚፈጠሩት የፖለቲካ እድሎች ወሰን አይኖራቸውም። ስለዚህ ወደድነውም ጠላነውም፣ ከኦነግ ጋር መነጋገርና መተባበር በሳልነት ነው፤…"

ከዚህ አባባላቸው ግልጽ ባያደርጉትም የኦነግ ውስጣዊ ችግር "ኦነግ ጥያቄያችን በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት ውስጥ መፈታት ይኖርበታል በሚል ወገንና አይ አቋማችን እንደበፊቱ ቅኝ ከያዘችን ኢትዮጵያ መገንጠል ነው" በሚለው ወገን ይሁን ሌላ ውስጣዊ ችግር ግልጽ ባያደርጉትም እንደ ውስጠ አዋቂነታቸው ግን የኦነግን በኤርትራ (በሻቢያ) ቁጥጥር ስር ያለ መሆኑን በጽሁፋቸውም በድጋሚም በፓል ቶክ ውይይታቸው ገልጸውታል። ዶር ጌታቸው እዚህ ጋ ያቀረቡት ችግር ነው አንደኛው ጥያቄያችን። በሻቢያ ጥገኝነትና ቁጥጥር ስር ያለ ማንኛውም ድርጅት ለሀገራችን አይበጃትም፣ መዘዙ ብዙ ነው ስንል የሻቢያን ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ መበታተን ሌት ተቀን የሚፈጋ ኃይል በመሆኑ ነው። ሕአወትን ገና ከምስረታው ቀፍቅፎና አጎልብቶ ሀገራችንን ለዘር ፖለቲካ ከማብቃቱም በላይ ወደፊትም የሌሎች መበታተን ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የግንጠላ አንቀጽን በሕገ መንግሥት ላይ ይሰፍር ዘንድ ትልቁን ሚና በስተጀርባ የተጫወተ ሻቢያ ነው። ሻቢያ ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ ሀገር እንዳትቀጥል (ለጊዜው ከወያኔ በጥቅም ቢጋጭም) የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ለዚህም በሀገራችን የሚንቀሳቀሱትን ተቃዋሚ ድርጅቶች ለማጥመድና መጠቀሚያ ለማድረግ ከመጣር ወደ ኋላ እንደማይል ልንገነዘብ ይገባናል። ይህ የኦነግና ኦብነግ ሻቢያ ጉያ ከመወሸቅ አልፎ፣ ይዘው የተነሱት ዓላማ ለሻቢያ የሚያመቸው፣ ኢትዮጵያን በየአቅጣጭው ለመበታተን ነውና ነው ተቃውሟችን። ኦነግን በአደባባይ ይዞ "ወያኔን በመጣል ላይ ተባበሩን" ከመባሉ በፊት ያለው ችግር በጠረጴዛ ዙሪያ ይፈታና ስምምነት ላይ ሲደረስ ብቅ ማለቱ ተገቢ ነበር ነው ጥያቄው። የግንቦት 7 እና የኦነግ አመጣጥ ግን ከፈረሱ በፊት ጋሪው ሆነና ነው መደናበሩ።

ዶር ጌታቸው ስለ አንድነት ኃይሉና ስለ ኅብረት ጉዳይም የሚሉትን ብለዋል።

ገጽ 2፡ "በኢትዮጵያዊነት የተደራጁና ዛሬ "የአንድነት ኃይሎች" ነን የሚሉት በእውነት ከተመረመሩ በቦታው ላይ የሚገኙ አይመስለኝም።…የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍና ክብር ያለው አንድ ድርጅት ለናሙና እናቅርብ።"

ገጽ 3፡ "…በወያኔና በተለያዩ የዘር ድርጅቶች በኩል የተቃጡት የመገነጣጠል አደጋዎች በየጊዜው እየሰፉ ሲሄዱ፡ ኢትዮጵያን ሊከላከል የሚችል እውነተኛ የአንድነት ኃይል አሁን በእርግጠኝነት ጠንክሮ አልተደራጀም፤ በቦታው ላይ አይገኝም።…"

ታዲያ መፍትሄው ዳግም የመገንጠል ዓላማ ያላቸውን አስተባብሮ እነሱን ማዕከል ያደረገ ዳግማዊ "ኢሕአዴግ" ለመፍጠር መጣር ነው አስፈላጊው ጉዳይ? ወይስ የተዳከመውን የአንድነት ኃይል ችግሩን መርምሮ ሊጠናከር የሚችልበትን አቅጣጫና ትልም መተለም? የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ባማከለ መልኩ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታ ወያኔን ወደ ታሪካዊ መቃብሩ ከቶ በጋራ ለመጪው መንግስት መምከርና፡ እየታገሉ መዘጋጀት የሚኀለብትበትን መንገድ ምሁራንን፡ ሀገር ወዳድን፡ ታዋቂ ግለሰቦችንና ሚመለከታቸውን አሰባስቦ ይመክሩበትና ይጠናከሩ ዘንድ ማበረታታቱ ነው አስፈላጊው ወይስ የአንድነት ኃይል ተዳክሟልና ዘረኝነትን ማራገብ? "ወያኔ ቢወድቅ ለኦነግና ለኦብነግ ነው አመቺው ጊዜ በማለት" ለነሱ ታማኝነትን ለማሳየት የአንድነት ኃይሉን በማጥላላትና፡ በአንድነት ላይ በመዘመት የሚገኝ ትርፍ ቢኖር ኪሳራ ነው።

"የበግ ላት ይወድቅልኛል" ብላ እንደምትጠባበቀው፡  ለዚህ የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ የተዳፈነ እሳት አድፍጠው ያሉትን፡ የግንጠላ ዓላማ ያላቸውን የዘር ድርጅቶች በርቱ ማለቱ ነው አዋጭ ወይስ የአንድነት ኃይሉ ይሰባሰብ ዘንድ፡ ለሀገርና ሕዝብ ሲባል ልዩነቶቻቸውን አቻችለው ለጋራ ሀገርና ሕዝብ ደህንነት ይቆሙ ዘንድ ያለንን ጉልበትና አቅም መጨረስ?

ገጽ 9፡ "አዎ፤ የዘርና የኢትዮጵያ ባንዲራ እኩል ጎን ለጎን ሲታዩ ደስ የማይለን አንዳንድ ሰዎች ልንኖር እንችላለን።…"

ኢትዮጵያዊነት፡ ብሔራዊ ማንነት ስንል አንዱ መገለጫችን አረንጓዴ፡ ቢጫ፡ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ሲባል በባንዲራዋ ተገዥነትን ይጠይቃል። ባንዲራዋ ሲወጣና ሲወርድ በብሔራዊ መዝሙሯ ቆሞ ማጀብን ይጠይቃል። በየትኛውም ዓለም ክልል የኢትዮጵያ ኤምባሲ ባለበት፡ ድል በምናደርግባቸው የስፖርት ዓይነቶች፡ በብሔራዊ ባህላችን፡ በየስብሰባው፡ ከፍ ብሎ የሚውለበለበውና በፍቅር ዓይናችን የሚያርፍበት የነጻነት ዓርማችንን እንኳን እኛ ሌሎች ነጻ የወጡ የአፍሪካ ሀገሮች፡ ኢትዮጵያን የነፃነታቸው ተምሳሌት በማድረግ ባንዲራችንን በተለያየ አቀማመጥ ወስደው አክብረውታል (ጋና፡ ማሊ፡ ካሜሩን፡ ሴኔጋል መጥቀሱ በቂ ነው)። ይህንን ነው እንግዲህ ዶር ጌታቸው ሌሎች (በዘር የተደራጁት) የኢትዮጵያን ትተው የራሳቸውን ይዘው ቢወጡ ብለው ሊፈላሰፉ የሚጥሩት።

እኛ ደግሞ “የጀግኖች መኩሪያ ያንድነት ዓርማ፤ ሁሌም ይውለብለብ ሰንደቅ ዓላማ” እያልን እንጠብቀዋለን።

በጥቅሉ ዶር ጌታቸው በቨርጂኒያው ስብሰባ ማንንም ድርጅት አልወከልም፣ የፖለቲካ ፍላጎትም የለኝም ሲሉ ተደምጠዋል። እየጻፉና እየተናገሩ ያሉት ግን ከባለቤቶቹ የከፋ ተሟጋችነት ፖለቲከኛነት ካልሆነ ኢኮኖሚኛነት ይሆን?

ዶር ጌታቸው በጋሻው በራስ አሉላ አባ ነጋ የፓልቶክ መወያያ መድረክ ቀርበው ከሰጡት ማብራሪያ የተቀነጨበውን በጽሁፍና በድምጽ ቅጂ ቀርቧል። በዚህ ውይይት ወቅት ዶር ጌታቸው “ሕዝብ ይወስናል” የሚለውን በማያሻማ ቋንቋ መልሰውታል።

ኦነግ በ 1983 ዓ.ም. ወያኔንና ሻቢያን አጅቦ ኦሮሚያን በግርግር ሊያገኝ ቋምጦ ነበር። በዚያም ወቅት ኦነግ የሽግግር መንግስቱ ተካፋይ በመሆን በቀጣይነት ከወያኔ ጋር አብሮ ባጸደቀው አንቀጽ 39ኝ መሠረት የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል በሚለው ፈሊጥ ለኦሮሞ ሕዝብ ሪፈረንደም እንዲሰጥና ፍላጎቱን ከግብ ማድረስ ነበር ጥረቱ። ወያኔም ኢትዮጵያን ከሻቢያ ጋር በጋራ ሊቦጠቡጡ ከነበራቸው ትልም፣ የኦነግን አቅም በመገንዘብ ከሽግግር መንግሥቱ ተገፍቶ የሚወጣበትን ወጥመድ አመቻችተውለት ዛሬ አለበት ላይ ደርሷል።

ዛሬም ታዲያ ዶር ጌታቸው ይኸው ይደገም ነው የሚሉት። ከፓል ቶክ ምላሻቸው ይህንን እናገኛለን ኦነግ ከወያኔ ውድቀት በኋላ በ transition ኑ ይሳተፋል፣ ***የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ ይቀርብለታል፣ Federal State, Unitary State, Independent State የሚለው ይቀርብለትና የመምረጥ መብቱ ይጠበቅለት ነው።*** ይህ ነው እንግዲህ ግልጽ ሆኖ የወጣው የ ዶር ጌታቸው መልዕክት። “የምን አንድነት ኃይል፣ የአንድነት ኃይል የለም፣ እስቲ ንገሩኝ…” እያሉ የጻፉትም እንዴት ተደርጎ የአንድነት ኃይሉ በዚህ አሳፋሪ የታሪክ ድግምግሞሽ ዝግጅት ይተባበራቸዋል። በመሆኑም የአንድነት ኃይሉን ማጥቃትና ማጥላላት ከተቻለም ማዳከም አንደኛው ግባቸው ቢሆን ለምን? ብለን ልንደነቅ፣ ልንጠይቅ አይገባም።

በማጠቃለልም፣ ዶር ጌታቸው በጽሁፋቸውም ሆነ በፓል ቶክ ውይይታቸው በርካታ ጉዳዮች የተምታቱባቸው ይመስለኛል። ሰው ከሌላው ላይስማማ ይችላል የሳቸው ግን ከራሳቸውም መስማማት ያቃታቸው ይመስለኛል። ለዚህ አባባሌ ከብዙው ዋናውን ልጥቀስ፣ ***ኦነግ ተገንጥዬ ነፃ ኦሮሚያ አቋቁማለሁ የሚል official አቋም መኖሩን አላውቅም።*** ይላሉ በሌላ በኩል ደግሞ “የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል” ሪፈረንደም ይሰጠው ይሉናል። የኦነግ ትግል ነፃ ኦሮሚያ ማቋቋም ካልሆነ፣ ይህ አቋም ከሌለው ለምን መገንጠል አስፈለገ? ሌላ ልጨምር፣ በሻቢያ ጉያ የተወሸቀ ማንኛውም ድርጅት ለኢትዮጵያ መፍትሄ እንደማያመጣ ይገልጹና በተቃራኒው ከኦነግ፣ ኦብነግና ግንቦት 7 መተባበርን እንደግፍ ይሉናል። የሻቢያስ ጉዳይ እንዴት ሆኖ? ብለን የምንጠይቀው ለዚህ ነው። የመጨረሻ፣ ኦነግን ጠንካራና ብቸኛ የኦሮሞ ሕዝብ ወኪል መሆኑን በቨርጂንያው 100% ስሌታቸው የተናገሩትን

በፓል ቶክ ክፍል ደግሞ "የውስጥ ችግር አለበት፡ ተከፋፍሏል" ይሉንና እንደውም ሌላኛውን ወገን ጊዜው ያለፈበት፡ ሞኝ የያዘው ፈሊጥ እያሉ ያጥላሉታል። ታዲያ እኚህ የተምታቱ ሀሳቦች ከማነው ችግሩ ከራሳቸው ይመስለኛል። "ውብ" ቃናቸውንና አነጋገራቸውን ለሀገራቸው ኢትዮጵያ አንድነትና ለኢትዮጵያ ማንነት እንደተናገሩ፡ እንደዘመሩ፡ እንዳስተማሩ ቢወረፉበት፡ ቢሰደቡበት ይመረጣል። ወገኖቻቸው የሚሏቸውን ቆም ብለው ማድመጥ ካቃታቸው ኋላ አድማጭ እንዳያጡ እሰጋለሁ።

የጽሁፌ መቋጫ የዛሬ አራት ዓመት የAFD ምሥረታ ወቅት፡ ሐምሌ 14 ቀን 1999 ዓ.ም. "የሕዝብ ድምጽ ይከበር የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ" በሚል ርዕስ፡ በአቶ ተማቹ ለንባብ ቀርቦ ከነበረው፡ ከዛሬው ሁኔታ ጋር እንድታገናዝቡትና ዛሬስ? ብላችሁ ትጠይቁ ዘንድ በመጥቀስ ይሆናል።

"በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና በሕዝብ አንድነት ለምትገነባ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመሥረት ለሚሟገቱና ለሚታገሉ ኃይሎች የፖለቲካ ሥልጣን ማግኘት የማይመኙ ባዕዳን ኃይሎች በአለ አቅማቸው ድጋፋቸውን እስከተመቻቸው ድረስ ለወያኔ ይለግሳሉ። ደክሞም ከታያቸው ለሌላ አዲስ ጉልበት ላለው በታኝ ኃይል እገዛ ከማድረግ ወደ ኋላ እንዳላሉና እንደማይሉ እያየን ነው። ባዕዳን ኃይሎች ለጥቅማቸው ሲሉ ወያኔን ግፋበት፡ አይዞህ፡ በርታ ባዮች ከአፍሪካዊቷ ግብፅ ፡ ከአረቡ ዓለም ጀምሮ በለጸገን ያሉት አሜሪካና እንግሊዝ፡ ሀገራችንን የሸቀጥ ማራገፊያ ያደረገችውና የሀገራችንን የተፈጥሮ ሀብት ለመዛቅ እያለመች ያለችው ቻይና ሁሉ ሀገርን እየሸጠ፡ ወጣቶችን ለዘመናዊ ባርነት እያሰደደ፡ እየላከ፡ እየሸጠ ያለው ወያኔ ከሁሉም በላይ ተመችቷቸዋልና አሁንም ይመችህ ብለው ከመመረቅ፡ አነሰህ ብለው ከመለገስ፡ ግደልበት ብለው ጥይት ከማቀበል፡ አንድደው ብለው ክብሪት ከመጫር አይመለሱም። የወያኔ አገዛዝ በሂደት ቢያበቃለት እንኳ ቀጣዩ አራተኛ መንግሥት ሌላ ብሔር ይዞ፡ ሌላ ባንዲራ ተሸክሞ በአዲስ ኃይል፡ ሌላ በታኝ፡ ሌላ ከፋፋይ፡ በአዲስ መልክ የኢትዮጵያን መጥፋት ለሚመኝ ኃይል እያዘጋጁን መሆኑን ነጋሪና አስረጅ የሚያስፈልገው አለመሆኑን የትብብር ለአንድነትና ዲሞክራሲ (የAFD) ምሥረታና ዕቅድ በቂ ምስክር ነው።" የጥቅሱ መጨረሻ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

ቸር ይግጠመን

ነሐሴ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. (August 20, 2011)

አሉላ (alulla2@yahoo.com)

## አባሪ፡ <u>ከዶ/ር ጌታቸው ራስ አሉላ አባ ነጋ ቃለ ምልልስ ተቀንጭቦ የተወሰደ</u>

***"የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ ይቀርብለታል፡ Federal State, Unitary State, Independent State የሚለው ይቀርብለትና የመምረጥ መብቱ ይጠበቅለት ነው።" ዶር ጌታቸው በጋሻው።***

ዕሁድ ነሐሴ 8 ቀን 2003 ዓ.ም. (Agust 13, 2011) ከቀኑ 2 pm Eastern Time ጀምሮ ዶር ጌታቸው በጋሻው በራስ አሉላ አባ ነጋ የመወያያ ክፍል በቀረቡበት ወቅት ከአድማጮች ቀርቦላቸው ከነበረው ጥያቄና መልስ ውስጥ መሠረታዊ ነው ያልኩትን በጽሁፍና በድምጽ ቅጂ ያለውን አቅርቤላችኋለሁ። (ትኩረት የሚገባቸው ነጥቦች ላይ ሥርዝ የተጨመረበት)

***<u>ጠያቂ 1</u>*** ፡ ጥያቄዬ ዶር ጌታቸው በጋሻው በዚህ ሁለት ቀን የጻፉትን ጽሁፍ አንተርሶ ነው። ዶር ጌታቸው በጽሁፎ ላይ በደንብ አልገልጽም ምንድነው "…በኦነግ ውስጥ ብዙ የሚያበረታቱ ለውጦች…" እንዳሉ ይገልጻሉ። እነኚህን ዓይነት ሁኔታዎች "…አዲስ ኃይል፡ አዲስ አሰላለፍ፡ አዲስ ራዕይ፡…" እንዳለ ይገልጻሉ። የርሶ ጽሁፍ ከመውጣቱ ቀደም ብሎ በ9/8/11 ደግሞ የ Oromo Liberation Front ለ Secretary General of the United Nations በጻፈው ጽሁፍ ውስጥ እሱን ለጥቀስና ባጭሩ "The OLF is a legitimate organization leading the Oromo people's national struggle against the colonial regime of Ethiopia" ይላል። ይህ በአጠቃላይ በደብዳቤው መሠረት ኧ… ቅኝ ከያዘቻቸው ኢትዮጵያ እንደሆነ ትግሉን ይገልጹታል። ይህንን ደግሞ ለማስረገጥ ለተለያዩ የዓለም ክፍል ለ UK, France, Russia, Chania, Germany, US, እንዲህ በትነዋል:: እና በዚህ ሁኔታ ላይ ይህንን አሁን ከግንቦት 7 ጋር ንግግር ላይ ነን፡ አብረን እየታገልን ነን በሚሉበት time ላይ ይህንን እያወጡ ምኑ ላይ ነው ለውጡ?

***<u>ዶር ጌታቸው፡</u>*** በጣም አመሰግናለሁ ይሄ ጥያቄ ስላቀረብክልኝ፡ ኧ… እኔን ደግሞ በጣም ኧ…ኧ… Hich ኧ…ኧ… እያሳከከኝ ያለ፡ በዚህ ላይ እንዴት እናገራለሁ በሚለው፡ እና ጥሩ ነው፡ ወረቀቱን አይቼዋለሁ። ኧ…ኧ… በአቶ ዳእድ ይብሳ የተጻፈ በኦነግ ስም፡ እና በአሁኑ ጊዜ ነው Colonial Ethiopia ነው ሚለው፡ እና በጣም የሰለቸ conceptually ትክክል ያልሆነ፡ ድሮ! ኦነግ ሲመሠረት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ከዚህ በዌብ ሳይቱም ላይ የምታዩት ይመስለኛል፡ ምንም መሠረት የሌለው conceptually ትክክል ያልሆነ፡ ኧ…ኧ… ሞኝ የያዘውን አይለቅም ዓይነት ነገር ነው፡ እስከዛሬ ድረስ በዚህ ላይ እያሉ መሄዳቸው በጣም የሚያሳዝን ነው ይሄ ነገር። እና ለ ኧ…ኧ… ለself determination የምንታገል ነን በሚሉት ላይ ምንም ችግር የለኝም። ኧ…ኧ… ግን ይኼ የተጻፈው still Ethiopia colonialist በሚለው ደረጃ ያቀረቡት እኔ ከዚያ ሌላ ነው ነገሩ…። ጮክ ባለ ድምጽ፡ እኔ ይኼ…ይኼ…

ለምን በዌብ ሳይቱ ላይ ያለውን ፕሮግራማቸውን አልቀየረም ነው፡ እኔ እሱን እንግዲህ እነሱን ጠይቁ፡ አንደኛ ማነው ያንን ዌብ ሳይት የሚቆጣጠረው ነው። እንግዲህ ግልጽ ለማድረግ አቶ ዳውድ ይብሳ የሚመሩት አንድ wing አለ የOLF ፡ሌላ በኮሎኔ በጀነራል ከማል ገልቹ wing አለ። ይኸ በዚህ በጀነራሉ በኩል ካለው ሲመጣ አላየሁም። ከአቶ ዳውድ ይብሳ በሚመራው በኩል ነው። በአቶ ዳውድ የሚመራው ደግሞ አንድ ወጥ አመለካከት አለው ወይ? That እሱንም መጠየቅ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። እኔ እንዳለ ኦነግ በቃ ተለውጦ ቀርቧል ኡ…ኡ…አላልኩም። ጽሁፉ የሚያመለክተው በዛ ውስጥ፡ በኦነግ ውስጥ የተለየ አመለካከት እየመጣ ነው ይኼን ነው ማስቻል ያለብን ነው።

***ጠያቂ 1፡*** ከዚህ ጋር አያይዤ ደግሞ የምጠይቆት፡ "ኦነግ የራሱን ውስጣዊ ችግር…" ይላሉ፡ "የራሱን ውስጣዊ ችግር ተወጥቶና ከኤርትራ ቁጥጥር እራሱን አላቆ ብዙ ጊዜ ቃል የሚገባውን የትጥቅ ትግል ከጀመረ በሀገራችን ውስጥ በፖለቲካው ውስጥ ከፍተኛ ሚና…" እንዳለው ይገልጻሉ። እዚህ ጋ እንትን ልበልና ስለ ኤርትራ የገለጹት ከዚህ አባባሎ አሁንም ኦነግ በኤርትራ ሥር እንዳለ በኤርትራ ጥገኝነት ላይ እንዳለ ያም በሻቢያ ቁጥጥር ሥር እንዳለ ይናገራሉ። ስለ ሻቢያ ደግሞ ሲያወሩ "ሻቢያ ለኢትዮጵያ አንድነት ያልቆመ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል" መሆኑን በጽሁፎ ላይ በተደጋጋሚ ይገልጹታል። እና እነኚህን የተቃረኑ አባባሎች እንዴት ያስታርቋቸዋል?

***ዶር ጌታቸው፡*** ኤርትሪያ! አዎ ኦነግ እና ሌሎች ድርጅቶች እንጄ EPPF ኧ…ኧ…ብዙዎች እንረዳዋለን የሚሉት እኮ እዚያ ነው። ኧ…ኧ.. ብዙ ድርጅቶች አሉ፡ ኦብነግ ምን…ምን… ግንቦት ሰባት ግንኙነት አለው እንደዚህ ነው ይባላል፡ እኔ በዚያ ላይ በጣም ግልጽ ነኝ፡ ከEPLF ወይም ከሻቢያና ከአቶ ኢሳያስ መንግስት ጋር ማንኛውም ድርጅት የሚያደርገው ግንኙነት ለኢትዮጵያ ጉዳ እንጂ ጥቅም የለውም ብዬ የምከራከር ነኝ። That I do. ከነኚህ ድርጅቶች ጋር በዚህ ጽሁፌ ላይ ያሳየሁት ኦነግ እራሱን ከኤርትሪያ ነፃ ካወጣ ነው የሚለው።

***ጠያቂ 2፡*** ዶር ጌታቸው አንተ ላይ ነው ጥያቄ ያለኝ፡ በሕብረት ጥያቄ ላይ ኧ… በኢትዮጵያ አንድነት፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት እና የወያኔን መወገድ መሠረት ያደረገ ሕ…ሕብረት ነው መቋቋም ያለበት ትል ነበር። እነዚህ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ብለህ ነበር። ይህንን መተክል ዛሬም ትቀበላለህ ወይ? ይኸን principle ዛሬ በ OLF፡ በግንቦት 7 እና በ ONLF በኩል ከምታየው አካሄድ ጋር ይኼ principle ይጣጣማል ወይ?

***ዶር ጌታቸው፡*** ሦስቱን principles ኧ…ኧ… የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፡ የሲቪል liberties እና የወያኔ መወገድ እነኚህን ሦስቱን እኔ በጣም የማምንባቸው ናቸው። አሁንም ኧ…ሣቅ…ኧ…ኧ…እና በዚያም ነው የምገፋው።ኧ…ኧ… ***ይኼ ማለት በ…ኧ… ሌላው ሁሉ ኧ…ኧ…ደሞ በዛ ይገደዳል ማለት…ከመጀመሪያውኑ እንደ condition ተደርጎ ማለት አይደለም፡ የሚል ከዚያም ጋር አለ።***

***ጠያቂ 2፥*** ሌላው ነገር አሁን ስትናገር “በሕዝበ ውሳኔ የሚያስወስኑ ከሆነ ምንድነው ክፋቱ?” እነዚህ የOLFዎችን እና የመሳሰሉት ነገር ብለሃል። ኧ… OLF እና ONLF ሰዎች ደግሞ በየቦታው እየሄዱ የሚሉት “Yes እኛ ተስማምተን ለመሥራት ችግር የለብንም፡ ሙሉ መብታችንን የምትቀበሉ ከሆነ፡” ያም ማለት ***የራሳችንን ዕድል በራስ መወሰን፡ እስከመገንጠል*** ማለት ነው። clearly እንደሚናገሩት ***“Referendum እስከሰጣችሁን ድረስ ችግር የለም፡ ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመሥራት ይላሉ።”*** አንዳንድ ሰዎች Article 39ን በተግባር መተርጎም ነው። ይኼን ይላሉ፡ ይኼን አንተ ትቀበላለህ ማለት ነው ወይ? አሁን ስትናገር “ምንድነው በህዝበ ውሳኔ የሚወሰን ከሆነ፡ ክፋቱ ምንድነው?” ብለሃል፡ ትቀበላለህ ወይ? ***Referendum ለ OLF እና ለ ONLF ኢትዮጵያ ውስጥ ይሰጥ ብለህ ትቀበላለህ ወይ?*** ይኼስ ከአለፉት አቋሞችህና ከወያኔ ፀረ-ወያኔ ከሆነው አቋምህ ከArticle 39 ጋር እንዴት ይጣጣማል?

***ዶር ጌታቸው፡*** Referendum ን እቀበላለሁ። በነገራችን ላይ ኧ…ኧ… ***ኦነግ ተገንጥዬ ነፃ ኦሮሚያ አቋቁማለሁ የሚል official አቋም መኖሩን አላውቅም።*** ዌብ ሳይቱ ላይ ሂዱ Colonial Ethiopia ይላል፤ በእርግጥ Referendum ይላል። OK Referendum ምቀበልበት condition ግን ይህን ጥያቄ በሚያነሳ ሕዝብ ይኼ ሳይሆን በሽግግር ጊዜ፡ በቂ የሽግግር ጊዜ፡ በቂ የዝግጅት፡ የማስተባበር ጊዜ ከተሰጠ ይሄንን የማንቀበልበት፡ የህዝብን ውሳኔ የምንፈራበት ምንም ምክንያት የለም። ኢትዮጵያዊነት በዚያ የበለጠ ይጠናከራል፡ ሊያሸንፍ ይችላል ብዬ አምናለሁ። አሁን እያሉ ያሉት ምንድን ነው፡ በ transition ኑ እንሳተፉለን፡ ***የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ ይቀርብለታል፡ ኧ… Federal State, Unitary State, Independent State የሚለው ይቀርብለትና የመምረጥ መብቱ ይጠበቅለት ነው።*** እንግዲህ፡ ኢዲዮ! ኦነግ ሞቷል፡ ደካማ ነው፡ የኦሮሞ ሕዝብ ለመገንጠልም አይፈልግም የሚል ካመንስ፡ ለምንድነው ይኼን የምንፈራው?